ነሀሴ 20፣ 2008

ውድ የአር. ኤ. ዩ. ሢ ማህበረሰብ

ቀጣዩ የሪንጅ አቪኒው አፐር ካምፓስ አስተዳደር ሆኜ ስፅፍላችሁ ክብር ይሰማኛል.። የአስተዳደር ለውጥ የማህበረሰቡን ጥንካሬ እና የእድገት አካባቢዎችን ቆም ብለን እንድናስተውል ይረዳናል። በዚህ ሂደት አብረን እስክንሰራ ጓጉቻለሁ።

እንደሚታወቀው፣ በዘህ የስራ መደብ ስመደብ ላለፈው አመት በተለያዩ ወራቶች በአስተዳደርነት ፤ እንዲሁም ከሀያ አመታት በላይ የክልሉ የመለስተኛ ደረጃ መምህር እና የተግባር አሰልጣኝ ሆኜ ስላገለገልኩ፤ ስለ ትምህርት ቤቱ እና ክልሉ በቂ ዕውቀት አዳብሬያለሁ። መምህሮቻችን ተማሪዎቻችንን ለማገልገል የበቁ እና የታተሩ በመሆናቸው ፤ ቤተሰቦችም ተሳታፊ እና ተባባሪ በመሆናቸው ያየሁት አነሳስቶኛል። የአምስተኛ እመት የሁለተኛ ደረጃ መረሀ ግብር እንደመጀመሩ እና የክልሉ ካሪኩለም እንዲሁም አስተዳደራዊ ድጋፍ መዋቅር የመለስተኛ ደረጃውን ነፃና ጥራት ያለው እንዲሆን አድርጎታል። የምናሻሽልባቸው ዘርፎች ሁሌ ቢኖሩም፣ በአስፈለጊ ጊዜ ሁሉ ቆም ብሎ ለማሰብ በጎ ፈቃደኝነትን ሁልጊዝ እመለከታለሁ። ይህ ሰፊ ማህበረሰብ የተማሪዎቹን ትምህርት ከልቡ አናግቦ ወደፊት እንደሚጓዝ እምነቴ ነው።

የትምህርት ቤቱ አስተዳደር ሆኜ ከተሾምኩ በኋላ በክልሉ መገኘቴን በመጠቅም፤ መረጃዎችን ሰብስቤ፣ ውይይቶችን በማድረግ ለሰራተኞች ቅድሚያ የሚሰጡ ጉዳዮችን በጋራ ተመልክተናል። ከሰራተኞች ጋር በተደረገ የግል ውይይት ገጽታ፣ ለጋራ ተልዕኮ የሚሆን አንድነትን መሰረት ያረገ ፍላጎት ፈጥሯል። ይህም ፍላጎት በሰራተኞች የትምህርት ቤቱን ዋና አላማ መልሶ በመዳሰስ ላይ በተደረገ ዳሰሳ ተንፀባርቆ፣ ተማሪዎችና እና ቤተሰቦችም የዋና አላማው ተካፋይ እንዲሆኑ ግልፅ ሆኗል። እኔም የጋራ አላማ መጋራቱ ምን ያህል ለትምህርት ቤቱ ባህል እና የተማሪ ስኬት ቀና የሆነ አስተዋጽኦ እንዳለው ተመልክቻለሁ። መረጃ እና ልምድም ተስተውለው ውሳኔዎእ ሲደረጉ እንደ ኮኮብ ይጎላሉ። በዚህ ትልቅ ስራም ከሰራተኞች እና ከአር.ኤ.ዩ.ሲ ማህበረሰብ ጋር ለመስራት ደስ እያለኝ ነው።

በነዚህ ፈጣን ሁኔታዎች እና የክልሉ ባልደረቦቼ እርዳታ በመታገዝ ለመጪው የትምህር ዘመን የሚሆን መንደርደሪያ እቅድ አዘጋጅቻለሁ። እቅዱ የትምህርት ቤቱን ማህበረሰብ በጥልቀት እንድረዳ እና እዛ በታ ላይ ለመድረስ ይምወስዳቸውን እርምጃዎች የጊዜ መስመር ያሳያል። ይህ የጊዜ መስመር የተወሰኑ ቀድመው የተደረጉ እርምጃዎችም ጭምር ናቸው። በመጨረሻም፣ ይህ የመግቢያ እቅድ፣ መቼ እና እንዴት ከማህበረሰቡ የምማረውን በጋራ ስሜት የሚሰጡ ሀሳቦችን እንደምንካፍል ያካትታል።

ከእዳንዶቻችሁ ቀድሜ የማውቃችሁ ጋርም ለመገናኘት ጓጉቻለሁ። ለአር.ዩ.ሲ አዲስ ለሁናችሁት ደግሞ ለመተዋወቅ አዲሱ የትምህርት ዘመን ለሚያመጣቸው ትኩስ አይኖች እና ክፍት ልቦች መልካሙን ሁሉ እመኛለሁ።

ከምስጋና ጋር፣<br>
ጁሊ ክራቨን

## ጁሊ ክራሸን፣ ሪንጅ አቬኒው አፐር ካምፓስ
## 2009 የመግቢያ እቅድ

የአመቱ ትኩረት
እንደ አር.ዩ.ሲ ማህበረሰብነታችን፣ እኛ ማን ነን? እንዴትስ በጋራ እና በጥልቀት ለትምህርት ልቀት እና ለሁሉም ተማሪዎች የህብረተሰብ ፍትህ እንደግፋለን?

**ገዢ ግቦች**

- የአር.ዩ.ሲን ዋና እሴቶችን ማወቅ እንዱሁም እሴቶቹን ለመተግበር በተማሪዎች ውጤት በመታገዝ ለህብረተሰቡ ፍትህ መዋቅሮችን/ልምዶችን መስራት
- የሰራተኞችን አንድነት መፍጠር፣ የሙዊናትንና የመተባበርን ባህል መደገፍ
- የትምህርተ ቤቱን እና የቤተሰቦችን ህብረት መራት እና ማጠንከር
- የጋራ ውሳኔ መስጫ መዋቀሮችን መረዳትና ማጠንከር፤ የትምህርት አስተዳደር ቡድን (ትአቡ)፣ የተማሪ ድጋፍ ቡድን(ተድቡ)፣ የአር.ዩ.ሲ ቤተሰቦች (የአር.ዩ.ሲቤ)

**የአንድ ለ አንድ ቃለ መጠይቅ ጥያቄዎች**

- ከአር.ዩ.ሲ ውስጥ ለምን ዋጋ ትሰጣለህ/ትሰጫለሽ?
- በሚመጣው የትምህርት ዘመን ለትምህርት ቤቱና ለራስህ/ሽ ምን ተስፋ ታረጋለህ/ታረጊለሽ?
- ከአንድ ተማሪ ጋር የእንደገና እድል ቢኖረህ/ሽ፣ ምን ይሆናል? ለምን?
- ለምን ታስተምራለህ/ሪያለሽ?
- በማታስተምርበት/ሪበት ጊዜ ምን ማረግ ትወዳለህ/ጃለሽ?

**በክፍል ደረጃ ላሉ ተንከባካቢዎች ስብሰባ የተዘጋጁጥያቄዎች**

- ከአር.ዩ.ሲ ውስጥ በይበልጥ ለምን ዋጋ ትሰጣለህ/ትሰጫለሽ?
- ልጅህ/ሽ በጣም ስኬታማ የነበረበትን ክፍለጊዜ አስብ/ቢ። ስኬት ምን ይመስል ነበር? ያ ክፍለጊዜ እንዴት ልጅህን/ሽን እንደረዳው ንገረኝ/ሪኝ።
- ከትምህርት ቤቱ ጋር ባለው ግንኙነት በይበልጥ ምን ሰራልህ/ልሽ?
- የትምህርት ቤቱና የቤተሰቦች ትስስር ላይ እድገት የሚፈልገው የቱ ጋር ነው?

**ለክፍል ደረጃ ተማሪዎች የትኩረት ቡድን የሚቀርብ ጥያቄ፡**

- ከአር.ዩ.ሲ ውስጥ ምን ትወዳለህ/ጃለሽ?
- ስለአር.ዩ.ሲ እንዳውቅ የምትፈልገው/ጊው ምን ነገር አለ?
- በጣም ስኬታማ የነበርክበትን/የነበርሽበትን ክፍለጊዜ አስብ/አስቢ። ስኬት ምን ይመስል ነበር? በዛ ክፍለ ጊዜ ምን ስኬታማ ሊያገርግህ/ሽ ቻለ?
- ተማሪዎች እርስ በርስ እንዴት እንደሚቻቻሉ ከ1-5 ባለ ሚዛን መዝንልኝ/መዝኚልኝ? ምዘናው ይብራራ
- ከ1-5 ባለ ሚዛን ምን ያህል በይሉኝታ ሳትሰቀቅ/ቂ ሀሳብህን/ሽን ታካፍላለህ/ያለሽ? ምዘናውይብራራ